አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

**LION INTERNATIONAL BANK S.C.**

# አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

# የተሻሻለ የመመስረቻ ፅሑፍ

ታህሳስ 08 ቀን 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ

## የተሻሻለ የመመስረቻ ፅሑፍ

### መግቢያ

አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ (ከዚህ በኋላ ‹ባንኩ› እየተባለ ይጠራል) ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በ1952 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሰረት በመስራች ባለአክስዮኖች ፊራሚነት የመመስረቻ ፅሑፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ እንዲኖሩት ተደርጎ የተመሰረተ እና ስራዎችንም በዚሁ አግባብ ሲፈፅም ቆይቷል፡፡ ሆኖም፡-

- ሚያዚያ 4 ቀን 2013 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው የኢትዮጵያ የንግድ ህግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 የማናቸውንም አክስዮን ማሕበር የመተዳደሪያ ደንብ ሕጋዊ እውቅና የማይሰጥ በመሆኑ፤ባንኩ ደግሞ አጠቃላይ የአስተዳደርና የስራ አመራር አካላትን ተግባራትና ኃላፊነት እንዲሁም በባለአክስዮኖች መካከል እና በባለአክስዮኖችና በባንኩ መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን የሚወስን ዝርዝር የመተዳደሪያ ደንብ ያለው በመሆኑ እነዚህን የመተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች በመመስረቻ ጽሑፍ ውስጥ ማጠቃለል በማስፈለጉ፣
- ባንኩ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ በተደረጉ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች በማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በየጊዜው የተደረጉ ማሻሻያዎችን እና የተጨመሩ አዳዲስ ድንጋጌዎችን ሁሉ በማጠቃለል በአንድ የመመስረቻ ጽሑፍ ሰነድ ማዘጋጀት በማስፈለጉ፤
- በመመስረቻ ጽሑፉ ውስጥ የሚገኙ የሕግ ማጣቀሻ ድንጋጌዎች፣ ቃላትና ሐረጎችን ከአዋጅ ቁጥር 1243/2013 ድንጋጌ አንጻር ማስተካከያ ማድረግ በማስፈለጉ፣
- የባንኩ ባለአክሲዮኖች ታህሳስ 8ቀን 2015 ዓ.ም ባደረጉት 6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የባንኩ አደራጆች 1998 ዓ.ም ያፀደቁትን የማኅበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ድንጋጌዎች ከነማሻሻያዎቻቸው ጋር በአንድ ላይ ማጠቃለል እና በማሻሻል በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 400 (1) መሰረት አጽድቋል፡፡

### አንቀፅ 1

### የባንኩ ስም

የባንኩ ስም «አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር» ነው፡፡

### አንቀፅ 2

### የባንኩ ዋና ፅሕፈት ቤት

1. የባንኩ ዋና ፅሕፈት ቤት ኢትዮጵያ ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ የካ ክ/ከተማ ወረዳ 7 ሌክስ ፕላዛ ሕንፃ የቤት ቁጥር አዲስ ነው፡፡
2. ባንኩ እንደ አስፈላጊነቱ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጪ አገር ቅርንጫፎች ሊከፍት ይችላል፡፡

## አንቀፅ 3

## የባንኩ ባለአክስዮኖች

ባንኩ የባለአክስዮኖችን ስም ዝርዝር፣ አድራሻ፣ ዜግነት፣ የተከፈለና የተፈረመ የአክስዮን መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ ከዚህ መመስረቻ ፅሑፍ ጋር አባሪ ተደርጓል። ፡

## አንቀፅ 4

## የባንኩ የሥራ ዓላማዎች

በአጠቃላይ የባንኩ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

1. ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት አለው ብሎ በፈቀደው የገንዘብ መሰብሰቢያ ዘዴ ከህዝብ፣ ከንግድ ድርጅቶች እንዲሁም የመንግስት አካላት ተቀማጭ ገንዘቦችን መሰብሰብ፤
2. በተ.ቁ 1 ላይ በተቀመጠው መሰረት የተሰበሰበውን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ በብድሮች ወይም በኢንቨስትመንት ላይ ማዋል፤
3. በባንኩና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መካከል በሚደረግ ዝርዝር ስምምነት መሠረት ከመንግሥት ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል፤
4. በገንዘብ መልክ ያልተቀረፀ ወርቅና ብር እንዲሁም የውጪ ምንዛሬ የመግዛትና የመሸጥ፤
5. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚፈቅደው መሰረት የዋስትና ሠነዶችን፣ ዕንቁዎችን፣ የከበሩ ድንጋዮችን፣ ሌሎች ዋጋ ያላቸው ንብረቶች ተቀብሎ በአደራ በብረት ካዝናዎች ማስቀመጥ፤
6. ባንኩ በራሱም ሆነ በደንበኞቹ ስም ለሌሎች ሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ሰዎች ገንዘብ የማስተላለፍ፤
7. የኢትዮጵያ መንግስት የሚያወጣቸውን የሚተላለፉ የንግድ ሰነዶች፣ የገንዘብ ዋስትና ሰነዶች /ኔጎሼብል ሴኩሪቲስ/ መያዝ፣ መግዛት እና መሸጥ፤
8. በገንዘብ ማስከፈያ፣ በሐዋላ፣ እና በተስፋ ሰነዶች እንዲሁም በሌሎች የእዳ ማረጋገጫ ሰነዶች አማካኝነት በቅናሽ የማበደር እና የማስተላለፍ፤
9. የወኪል ባንኪንግ አገልግሎት መስጠትና የሌሎች ባንኮች እንደራሴ ወይም ወኪል መሆን፤
10. በዲጂታል ፋይናንስ፣ የክፍያ ስርዓት ኦፐሬተር ወይም በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የተለያዩ የፋይናንስ አገልግሎቶችን መስጠት፤
11. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ትርፋማ በሆኑ የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ መዋዕለ-ንዋይ ማፍሰስ፤ በራሱ ስምና በራሱ ሂሳብ በንግድ ድርጅቶች ውስጥ አክስዮኖችን መግዛት እንዲሁም አክስዮኖችን እንደአስፈላጊነቱ መሸጥ፤
12. የዋስትና ወይም የተያዥነት ውሎችን መስጠት፤
13. ሥራውን ለማካሄድ ገንዘብ መበደር፣ ለተበደረውም ገንዘብ ንብረቶቹን በዋስትና ለማስያዝ ለአበዳሪዎቹ ግዴታ መግባት፣ወይም ለአበዳሪዎቹ ማስተላለፍ።

14. የሚተላለፍ የምንዛሬ ወረቀቶችን፣ የክፍያ ትዕዛዞችንና የተስፋ ሠነዶችን በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጪ ማውጣት፣ መቀበል፣ መቀነስ፣ መግዛትና መሸጥ፤

15. ሌተር ኦፍ ክሬት ማውጣት፣ የባንኩ ጥቅሞች ሳይነኩ የሌሎች ባንኮችና ኢንቬስተሮች ወኪል ወይም ባለአደራ በመሆን ማገልገል እና በዚህም ኃላፊነት ለባንኮቹና ኢንቬስተሮቹም የውጭ ምንዛሬ መሸጥና መግዛት፤

16. የፋይናንስ ነክ ጉዳዮችን በተመለከተ የማማከርና የሥልጠና አገልግሎት መስጠት፣

17. በካፒታል ገበያ ውስጥ አክስዮኖችን እና ሌሎች ማናቸውንም የፋይናንስ ሰነዶች ወይም አገልግሎቶችን መግዛት፣ መሸጥ ወይም መሳተፍ እና ሕጉ የሚፈቅደውን ማናቸውንም አገልገሎት መስጠት፤

18. በብሔራዊ ባንክ የሚፈቀድለት በተለምዶ እንደባንክ ሥራ የሚታወቁ ሌሎች ተግባራቶችን ማከናወን፤

## አንቀፅ 5

## የባንኩ ካፒታል

1. የባንኩ የተፈቀደ ካፒታል ብር 3,000,000,000.00 (ሶስት ቢሊዮን ብር) ሲሆን፤ የተፈረመና ተከፈለ ካፒታል ብር 2,590,245,259.80 (ሁለት ቢሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሚሊዮን አራት መቶ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ብር ከ80/100) ነው::
2. የባንኩ ካፒታል ለመጨመር ወይም ለመቀነስ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሕጉ መሠረት ይፈፀማል::

## አንቀፅ 6

## ስለአክስዮኖች

1. ባንኩ ልዩ መብት የማያስገኙ መደበኛ አክሲዮኖች ተብለው የሚመዘገቡና ተመሳሳይ ዋጋ ያላቸው አንድ ዓይነት አክሲዮኖች ይኖሩታል::
2. ባንኩ ልዩ መብት የማያስገኙ መደበኛ አክሲዮኖች ተብለው የሚመዘገቡና ተመሳሳይ ዋጋ ያላቸው አንድ ዓይነት አክሲዮኖች ሲኖሩት የእያንዳንዳቸው ዋጋ ብር 1000.00 (አንድ ሺህ ብር) 2,590,245.00 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሺህ ሁለት መቶ አርባ አምስት) መደበኛ አክሲዮኖች ተከፋፍሏል::
3. ማንም ሰው ባለአክሲዮን ሆኖ ለመመዝገብ ቢያንስ 5 (አምስት) አክሲዮኖች መፈረም ይኖርበታል:: ሆኖም ይህ የቁጥር ገደብ የተሻሻለው የመመስረቻ ጽሑፍ እስከሚፀድቅበት ቀን ድረስ የተመዘገቡ ነባር ባለአክስዮኖች ወይም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ/ውሳኔ/ መሰረት የሚደረጉ ወይም ለባንኩ ሰራተኞች እና ለነባር ባለአክስዮኖች የሚደረጉ የአክስዮን ዝውውሮችን አይመለከትም::
4. በማናቸውም ባለአክሲዮን/ፈራሚ፣በተናጠልም ሆነ ወይም ከሌላ ሰው ጋር በአንድነት፣ ወይም እድሜው/ዋ ከ18 ዓመት በታች ሆኖ በመጀመሪያ ደረጃ ዝምድና በስጋ ከሚዛመደው/ዳት ጋር በመሆን

ግለሰብ ጋር በመሆን ከባንኩ የተፈረመ ካፒታል ውስጥአምስት ከመቶ (5%) በላይ አክሲዮኖችን መያዝ አይችልም፡፡

5. አክስዮኖች በግዑዝ አልባ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ሊወጡ ይችላሉ፡፡ የባለአክስዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ በሚወስነው መሰረት በወረቀት የወጡ አክስዮኖች በግዑዝ አልባ አክስዮኖች ሊተኩ ይችላሉ፡፡

6. በወረቀት የወጣ እያንዳንዱ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ ወይም በምክትል ሰብሳቢ ተፈርሞ የባንኩ ማህተም ያለበት ሆኖ፣ በገፁ ላይ የሚከተሉትን ዝርዝሮች መያዝ ይኖርበታል፡፡

    ሀ. የባንኩ ስም፣ የባንኩ ዋና መ/ቤትና ባንኩ የሚቆይበት ጊዜ፤

    ለ. የካፒታል መጠንና የአክሲዮን የወጣበት ዋጋ መጠን፣

    ሐ. የመመስረቻው ጽሑፍ የተፈረመበት ቀን እና ባንኩ በንግድ መዝገብ የተመዘገበበት ቀንና የምዝገባው ቦታ፣

    መ. የአክሲዮን መለያ (ሲሪያል) ቁጥር እና አክሲዮኑ መደበኛ ስለመሆኑን፣

    ሠ. የአክሲዮኑ ዋጋ በሙሉ ካልተከፈለ የተከፈለውን ገንዘብ መጠን ወይም ዋጋው በሙሉ ከተከፈለ ይህንኑ የሚያመላክት መግለጫ፣

    ረ. አክስዮኑ ለውጪ ዜጋ መተላለፍ የሚችል መሆን አለመሆኑ የሚያሳይ መግለጫ፣

7. የዳሬክተሮች ቦርድ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት የጠፋበት ባለአክሲዮን ለመጥፋቱ የሚያረጋግጥ ተዓማኒነት ያለው ማስረጃ ከሚመለከተው መንግስታዊ አካል ሲያቀርብ በጠፋው ምትክ አዲስ የአክሲዮን ምስክር ወረቀት ሊሰጠው ይችላል፡፡

8. የዳሬክተሮች ቦርድ በጠፋው ምስክር ወረቀት ምትክ አዲስ ምስክር ወረቀት ከመስጠቱ በፊት፣ ተገቢ ነው በሚለው መንገድ ባለአክሲዮኑ ስለመጥፋቱ ማስታወቂያ እንዲያወጣና በጠፋው አክሲዮን ምክንያት በባንኩ ላይ ሊቀርብ ለሚችል ክስ ባንኩ ለሚደርስበት ጉዳት የሚመጥን ዋስትና እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል፡፡

## አንቀፅ 7

## አክስዮኖችን ስለመመዝገብ እና ስለማስተላለፍ

1. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚፈቅደው ቅርፅና አካሄድ መሠረት፣ ባንኩ የባለአክስዮኖችን ዝርዝር የሚያሳይ መዝገብ በዋና መስሪያ ቤቱ ይይዛል፤ መዝገቡ የወረቀት ወይም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ቋሚ የኤሌክትሮኒክስ መዝገብ ሊሆን ይችላል፡፡

2. መዝገቡ የባለአክሲዮኖችን ስሞችና አድራሻዎች፣ ዜግነት፣ የአክሲዮኖችን መለያ ቁጥርና ብዛታቸውን፣ የተከፈለው ገንዘብ መጠን እና ባለአክሲዮኖቹ በመዝገቡ የተመዘገቡበትን ቀን መያዝ አለበት፡፡

3. መዝገቡን ማናቸውም ባለአክሲዮንና ማናቸውም የተፈቀደለት አካል ሊመለከተው እንዲችል በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት በመደበኛ የሥራ ሰዓት ሁሉ ክፍት መሆን አለበት፡፡

4. አክሲዮኖችን በዋስትና ማስያዝን ጨምሮ ለሌላ ሶስተኛ ወገንማዘዋወር ወይምበባለመብትነት ለሌሎች መስጠት በባንኩ ለዚሁ በተዘጋጀው መዝገብ ላይ መመዝገብ ያለበት ሲሆን፣ በአክሲዮኖች መዝገብ ላይ እስከሚተላለፍበት ጊዜ ድረስ ይዞታው በቀየው ባለአክሲዮን ይቀጥላል፡፡
5. እያንዳንዱ የተመዘገበ አክሲዮን ዝውውር ወይም ለሌላ ሰው ባለመብትነት መስጠት የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚያፀድቀው ቅፅ መሰረት በፅሑፍ መሆን አለበት፡፡

## አንቀፅ 8

## የባለአክሲዮኖች መብቶች እና ግዴታዎች

በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (ከነማሻሻያዎቹ) ፣ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እንዲሁም በሌሎችሕግጋትና የብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው፣ እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ከዚህ የሚከተሉትን የአክሲዮን መብቶች ይኖሩታል፡፡

1.1. በባንኩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔየመሳተፍ እና በአክስዮን መጠኑ ልክ ድምፅ የመስጠት መብት፤

1.2. በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በሚወሰነው የትርፍ ድልድል ድርሻመሠረት ከተጣራው ትርፍ የመካፈል መብት፤

1.3. እያንዳንዱ ባለአክሲዮን ባወጣው ካፒታል መጠን የሚሰላ ሆኖ፣ ባንኩ ፈርሶ ሥራ በሚያቆምበት ጊዜ ከንብረቱ ሽያጭ ከሚገኘው የተጣራ ገቢ ድርሻውን የማግኘት መብት፤

1.4. የጠቅላላ ጉባዔ ቃለ-ጉባዔዎችንና በጠቅላላ ጉባዔዎች ላይ የተገኙ አባላትን ዝርዝር የመመልከት መብት፣ የሂሣብ ሚዛንና እንዲሁም የትርፍና የኪሣራ ሂሣብ፣ የዳሬክተሮች ቦርድና የኦዲተሮች ሪፖርቶችን ቅጅዎች የመውሰድ መብት፡፡

1.5. የባንኩ ካፒታሉ በሚያድግበት ወቅት አዲስ ከወጡት አክሲዮኖች የመግዛት የቀደምትነት መብት፡፡

## አንቀፅ 9

## የባለአክሲዮኖች ተግባራት እና ኃላፊነት

1. የባንኩ ባለአክሲዮኖች ተግባርና ግዴታዎች አግባብነት ባላቸው በባንክ ሥራ አዋጅ ቁጥር 592/2000 (ከነማሻሻያዎቹ)፣ በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ እንዲሁም በሌሎች ሕግጋትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች የሚገዙ ይሆናሉ፡፡
2. የአክስዮን ባለይዞታዎች፣ የቀድሞ አስተላላፊዎች እና ለመግዛት የፈረሙ ባለአክስዮኖች ላልተከፈሉት አክስዮኖች ዋጋ ለባንኩ የአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸው፡፡ቀሪው ገንዘብ በተወሰነው ጊዜ ያልተከፈለ እንደሆነ ሕጋዊ ወለድ የመክፈል ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. አክሲዮኖቹ የተሰጡት በአባባ ጥቅም እንደሆነ፣ ባለአባባው የአባባው ጊዜ መብት ሲያልቅ የከፈለው ገንዘብ እንደሚመለስለት ለመጠየቅ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ባልተከፈለው የአክሲዮን ገንዘብ ጥሪው መሠረት ቀሪውን ገንዘብ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡

4. ማንኛውም ለመግዛት የፈረመ ሰው ወይም ባለአክሲዮን የሆነ ሰው የራሱ የሆነውን አክሲዮን ያስተላለፈ እንደሆነ ካስተላለፈበት ጊዜ ጀምሮ 2 (ሁለት) ዓመት ካለፈ በኋላ ላልተከፈለው ገንዘብ ሃላፊነት የለበትም፡፡

5. ቀሪውን ገንዘብ በተወሰነው ቀን ያልከፈለ ባለአክሲዮን ላይ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 289 ከንኡስ አንቀፆች 3 - 7 የተደነገጉት ተፈፃሚነት አላቸው፡፡

## አንቀፅ 10

## የማሕበሩ የአመራር አካላት

ባንኩየሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡፡

1. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ፤
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ፤
3. ዋና ሥራአስፈፃሚ፤
4. የማሕበሩ ፀሐፊ፤ እና
5. የውጭ ኦዲተሮች፤

## አንቀፅ 11

## የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ

1. የባንኩ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የባንኩ ከፍተኛ ውሳኔ ሰጭ አካል ነው፡፡
2. የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች መደበኛ ወይም አስቸኳይ ናቸው፡፡
3. የጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎችን ባለአክሲዮኖች በጉባዔው ባይካፈሉ፣ ባይስማሙ፣ ድምፅ መስጠት ባይችሉ ወይም መብት ባይኖራቸው በሁሉም ላይ ይፀናል፡፡
4. ማናቸውም ባለአክሲዮን እርሱ ሳይስማማ የአባልነት መብቶቹን መንፈግ አይችልም፡፡
5. የጠቅላላ ጉባዔዎችን ለመጥራት የሚችሉት አካላትና የአጠራሩ ሁኔታ በንግድ ህግ አንቀጽ 366 በተደነገገው አግባብ ይሆናል፡፡
6. የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሂሳብ አመቱ ከተዘጋ በኋላ ባሉት 6 (ስድስት) ወራት ውስጥ በዳይሬክተሮች ቦርድ መጠራት የሚኖርበት ሲሆን፤ ጉባዔው ቢያንስ በአመት 1 (አንድ) ጊዜ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም የዳይሬክተሮች ቦርድ ጉባዔውን የመጥራት ኃላፊነቱን ባልተወጣበት ጊዜ በኦዲተሮች፣ በፍርድ ቤት ወይም በሒሳብ አጣሪዎች ጥሪ ሊደረግ ይችላል፡፡
7. የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ በንግድ ህግ አንቀጽ 367 እና 370 የተደነገጉትን በሚያሟላ ሁኔታ መጠራት የሚኖርበት ሲሆን፤ በተለይም ጥሪው ሀገራዊ ስርጭት ባላቸው ሁለት ጋዜጣዎች እና በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ጥሪው ሊተላለፍ ይችላል፡፡
8. ምልዓተ-ጉባዔ ባለመሟላቱ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ መሰብሰብ ሳይችል የቀረ እንደሆነ ሁለተኛ ጊዜ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሰበሰብ የሚደረገው ጥሪ የሚደረገው የመጀመሪያው ጉባዔ በሚጠራበት ሰዓቱን እና የጊዜ ገደብ ነው፡፡

9. ምልዓተ-ጉባኤ ባለመሟላቱ የተነሳ አንድ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ መደረግ ሳይችል ከቀረ ሁለተኛና ካስፈለገም ለሶስተኛ የጉባዔ ጥሪዎች በአንድ ሳምንት ልዩነት ውስጥ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 366 እና 367 በተመለከተው መሰረት ይደረጋል፡፡

10. የጠቅላላ ጉባዔ የምልዓተ-ጉባኤና የድምፅ ብልጫን በተመለከተ በንግድ ሕጉ በአንቀፅ 398 እና 402 በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

11. ማንኛውም ባለአክስዮን በሌላ ባለአክስዮን ወይም ባለአክስዮን ባልሆነ ሰው ሊወከል ይችላል፡፡ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሚወስነውመሰረትየውክልና ስልጣንቅፁ፣ የሚቀመጥበት ስፍራና የጊዜው ገደብ በጥሪ ማስታወቂያው ውስጥ መገለፅ አለበት፡፡ ሆኖም የጊዜ ገደቡ ጉባዔው ከሚጀመርበት ከ3 (ሶስት) ቀናት በፊት መጠናቀቅ አይችልም፡፡

12. በእያንዳንዱ ጉባዔ ላይ በጉባዔው የተገኙ እና ያልተገኙ ባለአክስዮኖች የሚያሳይ የተሳታፊዎች የመመዝገቢያ ሰነድ መኖር አለበት፤ ሰነዱ በጉባዔው ላይ የተገኙት ወይም ወኪል የላኩትን ባለአክስዮኖች ስምና አድራሻ፣ ዜግነት፣ የተከፈለና የተፈረመ፣ ያልተከፈለ የአክስዮን መጠን እና የሚሰጠውን የድምፅ ቁጥር የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡ በጉባዔው ላይ የተገኙትን ባለአክሲዮኖች የተመዘገበበት ዝርዝር በተገኙት ባለአክሲዮኖች ወይም በወኪሎቻቸው የተፈረመበት ስለመሆኑ ጉባዔው ከመጀመሩ በፊት በማሕበሩ ፀሐፊ ይረጋገጣል፡፡

## አንቀፅ 12

## የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ስልጣን

የባንኩ የመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው የባንኩን ሀብትና ዕዳ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ ሂሣብ እንዲሁም የዳይሬክተሮችንና የኦዲተሮችን ሪፖርቶች መርምሮ ያጸድቃል ወይም ያልተቀበለው መሆኑን ያስታውቃል፡፡
2. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔውከዳይሬክተሮች ቦርድ የቀረበለትን የትርፍ ክፍፍል ተመልክቶ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች እንዲከፋፈል ይወስናል ወይም አግባብነት ያለውን ሌላ ውሳኔ ያሳልፋል፡፡
3. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን እና ኦዲተሮችን ይሾማል፤ ይሽራል፤ የስራ ዋጋቸውን ይወስናል፡፡
4. ባንኩ የእዳ ሰነዶችን (ዲቤንቸር) እንዲያወጣ ይፈቅዳል፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ ባንኩ ስለሚሰጠው ዋስትና ይወስናል፡፡
5. በአንድ ጊዜ ወይም የመጀመሪያ ሽያጭ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በተለያየ መጠን ከባንኩ ሀብት 51% (ሃምሳ አንድ በመቶ) ወይም ከዚያ በላይ የሚሆነውን መጠን ማስተላለፍን በሚመለከት ይወስናል፡፡
6. መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው በሕግ የአስቸኳይ ጉባዔው ሥልጣን ከሆኑት ውጭ ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ተወያይቶ ይወስናል፡፡

## አንቀፅ 13

## የአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ስልጣን

የባንኩ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. የባንኩ መመስረቻ ጽሑፍን ያሻሽላል፡፡
2. የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ ወይም ለመቀነስ በሚቀርብ ሃሳብላይ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡
3. የባንኩን ዜግነት ስለመለወጥ፣ ባንኩ እንዲፈርስ ወይም ወደሌላ አይነት የንግድ ማሕበር እንዲለወጥ፤ እንዲከፋፈል እና እንዲዋሃድ በሚቀርብ ሃሳብ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡
4. ሌሎች በሕግ ወይም በመመስረቻ ጽሁፍ በአስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲታዩ ተለይተው በተሰጡ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ያስተላልፋል፡፡

## አንቀፅ 14

## የጥቅም ግጭት

1. አንድ ባለአክስዮን በራሱ/በራሷ ወይም በሌላ ሶስተኛ ወገን ስም የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ወይም አንድ ባል/ሚስት ጥቅም በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከባንኩ ጥቅሞች ጋር የሚጋጭ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ይህ/ይህች አባል ድምፅ የመስጠት መብት/ቷን መጠቀም አይችልም/አትችልም፡፡
2. ዲሬክተሮች የራሳቸውን ተግባራትና ተጠያቂነቶች በሚመለከት ውሳኔ ላይ ድምፅ አይሰጡም፡፡
3. ምልዓተ-ጉባኤ በሚሰላበት ጊዜ በዚህ አንቀፅ ውስጥ ድምፅ የመስጠት መብት የተነፈጋቸው /የተከለከሉ/ አክሲዮኖች ከቁጥር ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡
4. ከዚህ ቀደም ብለው ባሉት በዚህ አንቀፅ በንኡስ አንቀፆች 1-3 የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው በባለአክሲዮኖች ጉባዔ ላይ ድምፅ በመስጠት መብት በነፃ መጠቀምን የሚቀንስ ማናቸውም ድንጋጌ አይፀናም፡፡

## አንቀፅ 15

## የዳይሬክተሮች ቦርድ

1. ባንኩ በጠቅላላ ጉባኤው በሚሰየሙና አስራ አንድ /11/ አባላት ባሉት የዳይሬክተሮች ቦርድ ይመራል፡፡
2. የዳይሬክተሮች ቦርድ አመራረጥን በተመለከተ አግባብነት ባላቸው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች ተፈፃሚነት አላቸው፡፡
3. የዳይሬክተሮች ቦርድ በንግድ ሕጉ፣ በዚህ የመመስረቻ ፅሑፍ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔዎች ለባንኩ ሌላ አካል (ሌሎች አካሎች) በተለይ ከተሰጡ ሥልጣኖች በስተቀር የባንኩ ድርጅታዊ ሥልጣኖች ይኖሩታል፡፡
4. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት የአንድ ዙር የአገልግሎት ዘመን 3 (ሦስት) ዓመታት ሲሆን፤ አንድ አባል መመረጥና ማገልገል የሚችለው ለሁለት ተከታታይ ዘመን ማለትም ለ6 (ስድስት) ዓመታት ብቻ ነው፡፡

5. የዚህ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመሪያ በሚፈቅደው መሰረት ለሥራ ቀጣይነት አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ 2 (ሁለት) የምርጫ ዘመን ያገለገሉት የቦርድ አባላትን ለተጨማሪ 1 (አንድ) ዙር እንዲመረጡ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ሊወሰን ይችላል:: ሆኖም ለተጨማሪ 1 (አንድ) ዙር የሚመረጡ የቦርድ አባላት ብዛትከጠቅላላ ቦርድ መቀመጫ ከ1/3ኛ (ከአንድ ሶስተኛ) መብለጥ የለበትም::
6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ከአባላቱ ¾ በተገኙበት ስብሰባ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢን እና ምክትል ሰብሳቢን በአብላጭ ድምፅ ይመርጣል::
7. የዳይሬክተሮች ቦርድ ወርሃዊ አበል እና ዓመታዊ የአገልግሎት ክፍያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣ መመሪያ መሰረት በባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ይወሰናል::
8. የብሄራዊ ባንክ መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ በንዑስ አንቀፅ 6 ላይ የተጠቀሰው የአገልግሎት ክፍያ የሚፈጸመው አመታዊ የተጣራ ትርፉ በዚያው ዓመት ለባለአክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ የሰጠ እንደሆነ ሲሆን፣ ዓመታዊው የአገልግሎት ክፍያው ለባለአክስዮኖች ከሚከፋፈለው የተጣራ ትርፍ 10% (አስር በመቶ) ሊበልጥ አይችልም::

## አንቀፅ 16

## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስልጣን እና ተግባራት

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ በንግድ ሕጉ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ፣ በመመሥረቻ ጽሑፍ እና በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔዎች መሰረት የተሰጡትን ተግባራት ያከናውናል::
2. በዚህአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከተሉትን ዝርዝር ተግባራት ያከናውናል::
   - 2.1 የባንኩ ዋና ስራ አስፈጻሚውን የቅጥር ሁኔታና ሌሎች ልዩ ልዩ አበሎችና ጥቅማ ጥቅሞችንም ይወስናል፤
   - 2.2 የባንኩ ዋና ስራ አስፈጻሚ እንዲሁም የውስጥ ኦዲት እና የሪስክ ማናጅመንት ከፍተኛ የስራ ክፍሎች የበላይ ኃላፊዎችን ይሾማል፣ ይሽራል፣ እንዲሁም ለሥራቸው የሚከፈለውን ክፍያ ይወስናል፤
   - 2.3 የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚያቀርባቸውን ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑ የባንኩ ምክትል ዋና ስራ አስፈፃሚዎችን እና የማሕበሩ ፀሐፊን ሹመት ያጸድቃል፤ የሥራ ሁኔታዎችንም እና ክፍያቸውን ይወስናል፤
   - 2.4 የባንኩን ድርጅታዊ መዋቅር፣ የሰው ኃይል ፍላጎትና የባንኩ የኦፐሬሽን፣ የአስተዳደርና የፋይናንስ ፖሊሲዎችን ያጸድቃል፤
   - 2.5 በንግድ ሕጉ እና በመመስረቻ ፅሑፍ ድንጋጌዎች መሰረት የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይጠራል፤

2.6 የባንኩ ባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔና የቦርድ ስብሰባዎች ቃለጉባዔ፣ የሒሳብ መዝገብ፣ የባለአክስዮኖች እና የዳይሬክተሮች መዛግብት እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች እንዲያዙ ያደርጋል፤ በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

2.7 ሕጉ በሚያዘው መሰረት የባንኩ የሂሣብ ሰነዶችና መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል፤ በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤

2.8 የባንኩን ሂሣቦች በባንኩ ኦዲተሮች እንዲመረመሩ ያደርጋል፡፡ ስለባንኩ የሂሣብ መግለጫ ዓመታዊ ሪፖርት ለባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል እና ያፀድቃል፤

2.9 የባንኩ ¾ (ሦስት አራተኛ) ካፒታል የጠፋ እንደሆነ የባንኩ ባለአክሲዮኖች መደበኛ ጉባዔ ሳይዘገይ ይጠራል፤

2.10 በሕግና በመመስረቻ ጽሑፉ መሰረት መያዝ ያለባቸውን መጠባበቂያ ገንዘቦች እንዲያዙ ያደርጋል፤

2.11 በባንኩ ስም በዋስትናም ሆነ ያለ ዋስትና ገንዘብ መበደርን ይፈቅዳል፤በባንኩ ስም የብድር ስምምነት ለመፈረም ዋና ስራ አስፈፃሚውን ይወክላል፤

2.12 የባንኩን ገንዘብ በሕግ በተፈቀዱ የኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ ያውላል፤

2.13 የባንኩ ቋሚ ሀብቶች መሸጥ፣መለወጥ፣ ማስተላለፍ፣ ባንኩ ለመግዛት የሚፈልጋቸውን ማናቸውንም የቋሚ ንብረት ግዥዎች መፍቀድ፣ የባንኩ የፋይናንስና ሌሎች ሰነዶች ማረጋገጥ፣ እነዚህን ውሳኔዎች ጨምሮ ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን በባንኩ ስም እንዲያከናውን ዋና ስራ አስፈፃሚውን ይወክላል፤

2.14 የውጪ ኦዲተሮችን ሹመት እና የአገልግሎት ክፍያ በተመለከተ ለመደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ያቀርባል፤ ያፀድቃል፤

2.15 በዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ በዋና ስራ አስፈፃሚ፣ በከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች እና በባንኩ መካከል የጥቅም ግጭት አለመኖሩን ይቆጣጠራል፤

2.16 በሌሎች በህግና በባለአክሲዮኖች ጉባዔዎች የተወሰኑትን ተግባራት ያከናውናል፤

3. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው ምክንያት ለሚደርሰው ጉዳት ለባንኩ በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

4. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት በተገቢው ጥንቃቄ እና ትጋት ስለመስራታቸው የማስረዳት ሸክም አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 17

## የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባ እና ውሳኔዎች፤

1. የዳይሬክተሮች ቦርድ በባንኩ ዋና መስሪያ ቤት ወይም ቦርዱ ስብሰባዎችን አስመልክቶ በሚያወጣቸው መመሪያዎች መሰረት ቢያንስ በወር 1 (አንድ) ጊዜ ስብሰባውን ያካሂዳል፡፡

2. የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎችን በሰብሳቢው ወይም ሰብሳቢው በማይኖሩበት ጊዜ በምክትል ሰብሳቢው እየተመራ ይካሄዳል፡፡ ነገር ግን ሁለቱም በማይኖሩበት ጊዜ በስብሰባው በሚሰየም በማናቸውም ዳይሬክተር ይመራል፡፡

3. የዳይሬክተሮች ቦርድ የተሰብሳቢዎችን ማንነት መለየት በሚያስችል እንዲሁም የአባላት ውጤታማ ተሳትፎን በሚያረጋግጥ መልኩ ስብሰባዎችን ቪዲዮ ኮንፈረንስ ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ማካሄድ ይችላል፤ የቦርድ አባላትም የቪዲዮ ኮንፈረንስ ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ስብሰባዎችን መሳተፍ ይችላሉ፡፡

4. ምልዓተ-ጉባዔ እና ድምፅ አሰጣጥን አስመልክቶ የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ወይም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በሚካሄዱ ስብሰባዎች የሚተላለፉ ውሳኔዎች ያለአንዳች ገደብ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

5. ማንኛውም ውሳኔ የሚተላለፈው ከዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት መካከል ውክልናን ጨምሮ 7 (ሰባት) ዳይሬክተሮች ሲገኙ ወይም ሲሳተፉ ነው፡፡ በቦርድ ስብሰባ ያልተገኘ ዳይሬክተር ሊወክል የሚችለውያልተገኘውን ዳይሬክተር ወክሎ በሚሳተፍ ሌላ ዳይሬክተር ነው፡፡

6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ የሚተላለፍ ሲሆን ድምፅ በተወካይ ሊሰጥ ይቻላል፡፡ ድምፅ እኩል በእኩል በሚከፈልበት ጊዜ የቦርዱ ሰብሳቢ የደገፈው ሀሳብ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

7. የቦርዱ ውሳኔዎች በቃለ ጉባኤ ተይዘው በስብሰባው በተገኙ ዳይሬክተሮችና በማሕበሩ ፀሐፊ መፈረም አለበት፡፡ ቃለ ጉባኤዎች በቃለ ጉባኤ መዝገብ ውስጥ ተመዝግበው ይቀመጣሉ፡፡

8. የዲሬክተሮች ቦርድ ውሳኔዎችን ለማድረግ አጋዥነቱ አስፈላጊ ነው ብሎ በገመተ ጊዜ ሁሉ በባለሙያዎች ምክር ሊረዳ ይችላል፡፡

9. የውሳኔዎች ቅጅዎች በሙሉ በሰብሳቢውና በፀሃፊው ይፈረማሉ፡፡

## አንቀፅ 18

## ዳይሬክተሮችን ስለመተካት

1. የዚህ መመስረቻ ጽሑፍ ደንብ አንቀፅ 14/1 እና 3/ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ በአንድ ሂሳብ ዓመት ውስጥ አንድ ወይም ከዚህ የሚበልጡ ዳይሬክተሮች በአንቀፅ 17.3 በተመለከቱት ወይም በሌላ በማንኛውም ምክንያት የለቀቁ እንደሆነ ያሉት ዲሬክተሮች ለቀሪው የሹመት ጊዜ የሚሸፍኑ ተተኪ ዳይሬክተሮችን በሕግ አግባብ መሰረት ሊሾሙ ይችላሉ፡፡ የተተኪ ዳይሬክተሮች ሹመት ለሚቀጥለው ጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ መፅደቅ ይኖርበታል፡፡ ጠቅላላ ጉባዔውም ሹመቱን ሊያፀድቅ ወይም በምትካቸው ሌሎች ዲሬክተሮችን ሊሾም ይችላል፡፡

2. በማናቸውም ጊዜ የዲሬክተሮች ቁጥር ከ7 (ሰባት) በታች በሚሆንበት ወቅት የባለአክስዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ በ 30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ ተጠርቶ አዲስ ዳይሬክተሮች ይሾማል፡፡

3. በሚከተሉት ምክንያቶች አንድ ዳይሬክተር ከዳይሬክተርነት ሊወገድ ይችላል፡፡

3.1. ዳይሬክተሩ ራሱ ወይም በዳይሬክተርነት ወይም በዋና ስራ አስፈፃሚነት የሚያገለግልበት ኩባንያ ሲከስር ወይም ዕዳ መሸፈን ሲሳነው፣ ወይም ዕዳውን ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ ሲወረስበት፤

3.2. አዕምሮው ትክክል ሳይሆን ወይም በወንጀል በሚያስከስስ ጥፋት ሲፈረድበት፣

3.3. ካለልዩ ፈቃድ በሂሳብ አመቱ ውስጥ በተካሄዱ የዳይሬክተሮች ቦርዱን ስብሰባዎችን ቢያንስ 75% (ሰባት አምስት በመቶ) መሳተፍ ካልቻለ፤

3.4. የዳይሬክተሮች ቦርድ የስነምግባር ደንብ ወይም የስብሰባ አካሄድ ስርዓት ላይ በተጠቀሱ ሌሎች ማንኛውም ምክንያቶች፤

## አንቀፅ 19

## የዋና ስራ አስፈፃሚ ስልጣን እና ተግባራት፤

1. ባንኩ በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሾም አንድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሚኖረው ሲሆን፤ ዋና ስራ አስፈጻሚ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች እና ከኃላፊነት ስለመታገድ ዝርዝር ሁኔታዎች በባንክ ስራ አዋጁ እና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት የሚወሰን ይሆናል፡፡

2. የባንኩ ዋና ስራ አስፈጻሚ በባንኩ የዳይሬክተሮች ቦርድ የሚወሰኑትንና የሚሰጠውን አጠቃላይ አመራር ተከትሎ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡፡

   2.1. ባንኩ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት፣ ከመንግስታዊና የግል ድርጅቶች እንዲሁም ከሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ጋር የሚያደርገውን የሥራ ግንኙነት ይወክላል፡፡

   2.2. ከዳይሬክተሮች ቦርድ በሚሰጠው ውክልና መሰረት የባንኩን ቋሚ ሀብቶች ይገዛል፤ ይሸጣል፣ ይለውጣል፣ ያስተላልፋል፤ ባንኩ ለመግዛት የሚፈልጋቸውን ማናቸውንም የቋሚ ንብረት ግዥዎች ይፈጽማል፤ ባንኩን የሚመለከቱ ሰነዶች ያረጋግጣል፤ የቋሚ ንብረቶችን የስም ማዘዋወር ጨምሮ ሌሎች ህጋዊ ተግባራትን በባንኩ ስም ያከናውናል፤

   2.3. የባንኩ የሚንቀሳቀሱ ሀብቶች ይሸጣል፣ ይለውጣል፣ ያስተላልፋል፣ እነዚህን ህጋዊ ተግባራት ለማስፈፀም በባንኩ ስም የሚያከናውኑ ኃላፊዎች ወይም ሰራተኞችን ይወክላል፤

   2.4. የባንኩን ደንቦችና ሥነ-ስርአት ህግጋትን (Bank Policies) አርቅቆ የዲሬክተሮች ቦርድ እንዲያፀድቃቸው ያቀርባል፤

   2.5. የባንኩን የኦፐሬሽን፣ የአስተዳደር፣ የሰው ሃይልና የፋይናንስ ፖሊሲዎችን አርቅቆ የዲሬክተሮች ቦርድ እንዲያፀድቃቸው ያቀርባል፤

   2.6. የዳይሬክተሮች ቦርድ ያወጣቸውን ፖሊሲዎች ተንተርሶ የሚወጡ የባንኩየአሰራር ደንቦች እና የሥነ-ስርአት ሕጎችንያፀድቃል፤

   2.7. ተጠሪነታቸው ለእርሱ የሆኑ የባንኩን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በመምረጥ ሹመታቸው በዳይሬክተሮች ቦርድ እንዲጸድቅ ያቀርባል፤

2.8. የባንኩ የሂሣብ አያያዝ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

2.9. የባንኩን ዕለት ከዕለት ሥራ ለማከናወን የአመራር ስብሰባዎችን ይጠራል፣ ኮሚቴዎችንም ያቋቁማል፣ ለሥራ ኃላፊዎችና ለሰራተኞች ውክልና ይሰጣል፤

2.10. በባንኩ ስም ወኪሎችን፣ የህግ አማካሪዎች፣ ነገረፈጆች እና ጠበቆች በመሾም የውክልና ሥልጣን ይሰጣል፤

2.11. በሕግና በዚህ የመመስረቻ ፅሑፍ ደንብ በደነገጉት መሠረት የመጠባበቂያ ገንዘብ ሂሣቦች ያቋቁማል፤

2.12. በባንኩ ስም በሌላ ባንክ ወይም ባንኮች ላይ ማንኛውም አይነት የባንክ ሂሣቦችይከፍታል፣ ያንቀሳቅሳል፤

2.13. የሐዋላ ሰነዶችን፣ ቼኮችን፣ የሂሳብ ሠነዶችን፣ የምንዛሪ ሠነዶችን፣ የተፃፉ ሰነዶችን፣ ሌሎች የስምምነት ሠነዶችንና እንዲሁም የገቢና የወጪ ሠነዶችን ይፈርማል፣ ይቀበላል፣ ወጪ ያደርጋል፣ ያዘጋጃል፣ ሥራ ላይ ያውላል፣ያፀድቃል፣ ቅናሽ ያደርጋል።

2.14. ባንኩን ከኪሣራ፣ከጥፋት፣ከድንገተኛ አደጋና ከማንኛውም ተጠያቂነት ለመጠበቅ የሚያስችል የመድን ዋስትና ከማንኛውም የመድን ኩባንያ ጋር ተፈራርሞ ያስገባል፤

2.15. የዳይሬክተሮች ቦርድ አስቀድሞ በሚወሰነው መሰረት በባንኩ ዓላማዎችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተራፊ ገንዘብን በልማት ሥራ ላይ ያውላል፤

2.16. በእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ሥራዎችን በወቅቱ በማጠናቀቅ፣የባንኩን የሂሣብ ሚዛንና የትርፍ የኪሣራ ሂሣብ በማዘጋጀትለዳይሬክተሮች ቦርድ ያቀርባል፤

2.17. ለቦርድ ስብሰባዎች አጀንዳ ከቦርዱ ሰብሳቢና ከማሕበሩ ፀሐፊ ጋር በመመካከር ያዘጋጃል፤

2.18. ከቦርድ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር የዳይሬክተሮች ቦርድ ስብሰባዎች እንዲጠራ ያደርጋል፤

2.19. በአጠቃላይ በዚህ ሠነድ በተለይ ያልተጠቀሱም ቢሆን ለባንኩ ሥራና ለዓላማዎቹ መሳካት አስፈላጊ የሆኑ ማናቸውንም ሥራዎች ያከናውናል፤

3. ዋና ስራ አስፈፃሚው ከላይ ከተሰጡት ሥልጣናት ውስጥ በከፊልም ሆነ በሙሉ ለሌሎች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

## አንቀፅ 20

## የማሕበሩ ፀሐፊ ስልጣን እና ተግባራት፤

1. ባንኩ ለዋና ስራ አስፈጻሚ ተጠሪ የሆነ የራሱ ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን፤ ቅጥሩም እና ስንብቱ በዋና ስራ አስፈፃሚ አቅራቢነት በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚፀድቅ ይሆናል።

2. የማሕበሩ ፀሐፊ በንግድ ሕግ አንቀጽ 341 እና 342 ስር የተዘረዘሩትን ስልጣን እና ተግባራት እንዲሁም ተጠያቂነት የሚኖረው ሲሆን፤ ከዚህም ባሻገር በባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና በዳይሬክተሮች ቦርድ የሚሰጡትን ሕጋዊ ተግባራት የሚያከናውን ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 21

## የባንኩ የውጭ ኦዲተሮች

1. የባንኩ የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ተቀባይነት ያላቸውን ኦዲተሮች ይሾማል፡፡
2. በዚሁ ሁኔታ የተሾሙት ኦዲተሮች የስራ ዘመን3 (ሶስት) የሂሳብ አመት ሂሳብ ማጠቃለያ ጊዜ ድረስ ነው፡፡
3. ኦዲተሮች ስለዘገባ፣ የንብረት ግዴታ አተማመንና የመሳሰሉትን በተመለከተ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣቸውን የኦዲተር አነስተኛ የሥራ ደረጃ መስፈርትን ጠብቀው ተግባራቸውን በጥንቃቄ ማከናወን አለባቸው፡፡
4. የኦዲተሮች ሪፖርትከባንክ የሂሳብ ዓመት ማብቂያ በኂላ ከዘጠና (90) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ይላካል፡፡
5. ኦዲተሮች በንግድ ሕጉ አንቀጽ 348 እና 352 ስር የተዘረዘሩትንኃላፊነት እና ተግባራት እንዲሁም ተጠያቂነት ይኖራቸዋል፡፡

## አንቀፅ 22

## ለማሕበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች መዝገብ

1. ባንኩ በዋና መስሪያ ቤቱ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን፣ የዋና ስራ አስፈፃሚ፣ የኦዲተሮችን፣ የማሕበሩ ፀሐፊንና በፌዴራል የቤተሰብ ሕጉ መሰረት ከነዚህ ጋር የሥጋና የጋብቻ ዝምድና ያላቸውን ሰዎች የግል ሁኔታ፣ ሙያቸውን፣ በሌሎች የንግድ ማህበራትና ድርጅቶች ያላቸውን ጥቅም፣ ስራ፣ የቦርድ አባልነት ወይም ሌላ ኃላፊነት ካላቸው ይህንኑ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የሚያሳይ መዝገብ መያዝ አለባቸው፡፡ ዳይሬክተሩ የንግድ ማሕበር የሆነ እንደሆነ የንግድ ስሙና የዋና መስሪያ ቤቱ አድራሻ ማሳየት አለበት፡፡
2. የሚመለከተው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል፣ ኦዲተር እንዲሁም የማሕበሩ ፀሐፊ መዝገቡ ውስጥ በሰፈሩት ጉዳዮች ላይ ለውጥ መደረጉን ካወቀ ይህንኑ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ 15 (አስራ አምስት) ቀናት ውስጥ ለባንኩ ዋና መስሪያ ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡
3. ባለአክስዮኖች እና የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤት ተወካዮች መዝገቡን በነፃ ማየት ይችላሉ፡፡ ባለአክስዮን ያልሆኑ ሰዎች ለዚህ የተወሰነውን የአገልግሎት ክፍያ በመፈፀም መዝገቡን የማየት መብት አላቸው፡፡

## አንቀፅ 23

## ስለባንኩ ሒሳቦች

1. የባንክ ስራ አዋጅ፣ የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣቸው መመሪያዎች የሂሣብና የመዛግብት አያያዝ በተመለከቱ ድንጋጌዎች በባንኩ ሂሣብ አያያዝና አመዘጋገብም ላይ ተፈፃሚ ናቸው፡፡
2. ባንኩ በተለይ የሚከተሉትን የማከናወን ኃላፊነት አለው፤
   - 2.1. ባንኩ በባንኩ ሥራ አዋጅ መሠረት መሥራቱን ለማወቅ የሚያስችሉ የባንኩ ሥራ እንቅስቃሴዎቹንና ያለውን የገንዘብ አቅም ግልፅ በሆነና በትክክል ሁኔታ የሚያስረዱ መዝገቦችን በአግባቡ መያዝ፤
   - 2.2. ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለባንኩ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ እና የፋይናንስ ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት መላክ እና እንደዚሁም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ስለባንኩ ሁኔታ ጥርጣሬ አድሮበት መረጃ በሚጠየቅበት ጊዜ አስፈላጊ መረጃዎችን መስጠት፤
   - 2.3. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ለሚያደርገው ምርመራና ቁጥጥር ሁሉ በማናቸውም ጊዜ ዝግጁ ሆኖ መገኘትና ከምርመራውና ቁጥጥሩ በኋላም ብሔራዊ ባንኩ የሚወስናቸውን እርምጃዎች ተግባራዊ ማድረግ፡፡

## አንቀፅ 24

## ሂሣብ ዓመት

የባንኩ የሂሳብ ዓመት እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ይሆናል፡፡

## አንቀፅ 25

## ዓመታዊ ሪፖርት

1. በእያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት ማብቂያና ከላይ በተመለከተው አንቀፅ 14(2.8) መሠረት ለሚቀርበው ሪፖርት የዳይሬክተሮች ቦርድ፡
   - 1.1. የትርፍና ኪሳራ ዝርዝር መግለጫ፣ የንብረት ቆጠራና የንብረትና የዕዳ ግምት ያዘጋጃል፡፡
   - 1.2. እንደዚሁም ያለፈውን የሂሳብ ዓመት የሂሣብ ሚዛንና የትርፍና ኪሳራ ሂሣብ መግለጫ በተጨማሪም ባንኩ ባለፈው የሂሳብ ዓመት ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎችን የነበሩት ጉዳዮች የሚገኩበትን ሁኔታ የሚያሳይ ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡
   - 1.3. ሪፖርቱ ትርፍና ኪሳራ፣ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት፣ ለዋና ስራ አስፈፃሚ እና ለኦዲተሮች የተከፈለ ጠቅላላ ክፍያ፣የተሰጠ ብድር ወይም የተገባ ዋስትና የሚያመላክት መግለጫ፤ እንዲሁም ስለመጠባበቂያ ገንዘብ ምደባና ስለዓመታዊ ትርፍ አደላደል ሃሣቦችን ማቅረብ አለበት፡፡

## አንቀፅ 26

## የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲተሮች ማቅረብ

የንብረት ቆጠራ፣ ሂሣብ ሚዛን፣ የትርፍና ኪሳራ ሂሣብና የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርትለዓመታዊ ጠቅላላ ስብሰባ ጥሪው ከመላኩ ቢያንስ ከ40 (አርባ) ቀናት አስቀድሞ ለኦዲተሮች እና ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ማቅረብ አለባቸው።

## አንቀፅ 27

## መጠባበቂያ ሂሣብን ስለመያዝ

1. ባንኩ በማናቸውም ጊዜ፡
   ሀ. በብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሰረት ባንኩ የካፒታሉን የመጠባበቂያ ግዴታዎች ይይዛል።
   ለ. ዓመታዊ የትርፍ ክፍያ ድርሻ ከመገለፁ አስቀድሞ ከዓመቱ ትርፍ ላይ ታክስ ተነስቶለት ከሚቀረው የተጣራ ትርፍ ላይ ከሀያ አምስት በመቶ (25%) ያላነሰ ገንዘብ በመቀነስ ወደ ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሳቡ ያዛውራል። ሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብ ከባንኩ ገንዘብ (ካፒታል) ጋር እኩል ሲሆን ከተጣራ ትርፍ ባንኩ በየዓመቱ ለመጠባበቂያ የሚይዘው መጠን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እንዲሆን ያደርጋል።
   ሐ. ያልተከፋፈለ ትርፍ፣ የተያዘ ገቢና ሌሎች መጠበባቂያዎች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይፈፅማል።
2. ባንኩ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት መጠባበቂያዎች ውጪ በባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የተወሰነ ከተጣራ ትርፉ ላይ ተቀናሽ የሚሆን መጠባበቂያ ገንዘብ ሊይዝ ይችላል።
3. ከሕጋዊ መጠባበቂያ ሂሣብ ተቀናሽ ማድረግ ወይም በመያዣነት መስጠት አይቻልም። ሆኖም የባንኩ ካፒታል ለማሳደግ ሲባል በሕጉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያዎች መሰረት ለካፒታል ማሳደጊያነት ማዋል ይቻላል።

## አንቀፅ 28

## በጥሬ ገንዘብ ተለዋጭ የሚሆን አነስተኛ ንብረትና የመጠባበቂያ ገንዘብ ሚዛን፤

ባንኩ፡-

1. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚወሰን መሠረት ባንኩ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በላከው ወርሃዊ መግለጫ ከተመለከተው ተቀማጭ ገንዘብና ካለበት ተመሳሳይ የህዝብ ዕዳ ባንኩ ለህዝብ ካለበት የግዴታ መጠባበቂያ ይይዛል።
2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በየጊዜው በሚያሰላው ልክ ባንኩ በጠቅላላ ያለበት የተቀማጭ ገንዘብ ዕዳ በመቶኛ የሚሆን የመጠባበቂያ ገንዘብ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዘንድ ያኖራል።

## አንቀፅ 29

## በቸልተኝነት ወይም እምነት በማጉደል ለሚደርሱ ኪሣራዎች መጠባበቂያ፤

ባንኩ፡-

1. ከዳይሬክተሮች በማናቸውም በሥራ አስኪያጅ፣ በዋና ኃላፊ ወይም በማንኛውም ኃላፊ ወይም ሠራተኛ ቸልተኝነት ወይም እምነት ማጉደል ለሚደርስ ኪሣራ መሸፈኛ የሚሆን ልዩ መጠባበቂያ ገንዘብ ይይዛል፡፡
2. ከእንደዚህ ዓይነቱ ኪሣራ ለመዳን ሲል በዚሁ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ተሰጥቶት እንደዚህ ዓይነት ከመሰለ ኪሣራ የሚያድን ዋስትና በመስጠት ሥራ ላይ በተሰማራ የመድን ድርጅት ዘንድ የመድን ዋስትና ይገባል፡፡

## አንቀፅ 30

## ትርፍ አደላደልና አከፋፈል

1. የባንኩ ዓመታዊ ትርፍ ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈለው በትርፍ ክፍያ ወቅት ባላቸው የተከፈለ የአክሲዮን መጠን ይሆናል፡፡የክፍያው ቀንና ሁኔታ በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ይወሰናል፡፡
2. የትርፍ አከፋፈል የባንኩ ኦዲተሮች በመረመሩትና የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ ባፀደቀው የተጣራ ትርፍ ላይ የተመሠረተ ሆኖ በአንድ ክፍያ ተፈፃሚ ይሆናል፤ ለክፍፍል የሚሆነው የተጣራ ትርፍ ከሂሣብ ዓመቱ ትርፍ ላይ ያለፈውን ዓመት ኪሳራዎችና ማናቸውም የተቀማጭ ገንዘብ ክፍያዎች ከተቀነሱ በኂላ የሚቀረው ነው::
3. ከላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪየባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በልዩ ሁኔታ ከመጠባበቂያ ገንዘብ ተቀናሽ ተደርጎየትርፍ ክፍፍል እንዲከፈል ሊፈቅድ ይችላል፡፡ የጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔም ለትርፍ ተከፋይ የሚሆኑት ገንዘቦች ከየትኛው መጠባበቂያ ገንዘብ ላይ እንደሚወሰድ በግልፅ ማመልከት ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ 31

## የሂሣብ ሚዛን መግለጫ ማውጣት

1. በባለአክስዮን ጠቅላላ ጉባዔ የፀደቀው የባንኩ የሀብትና እዳ መግለጫ አንድ ቅጂ እንዲሁም ጉባዔው መግለጫውን ያፀደቀበት ውሳኔ ቃለጉባዔ አግባብ ያለው ክፍል የሀብትና እዳ መግለጫው በፀደቀ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው የመንግስት አካል መላክ እና በባንኩ ድረገፅ ላይ መውጣት አለበት፡፡
2. የባለአክስዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ በተካሄደ በ2 (ሁለት) ሳምንታት ውስጥ ባንኩ፡-
   - 2.1. በኦዲተሮች የተመረመረ ሪፖርትና የስራ እንቅስቃሴውን የሚያሳይ የሂሳብ ሚዛን እና የትርፍና ኪሳራ መግለጫዎች በሁሉም የባንኩ የስራ ቦታዎች፣ ቅርንጫፎች እና ንዑስ ቅርንጫፎች ግልፅ በሆነ ቦታ ያስቀምጣል፡፡

2.2. የሂሳብ ሚዛን እንዲሁም የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ማብራሪያ ፅሁፎችን አባሪ በማድረግ ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ላይ ያሳትማል፡፡

## አንቀፅ 32

## የባንኩ የሥራ ዘመን

ባንኩ ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሟል፡፡

## አንቀፅ 33

## ስለባንኩ መፍረስና መዋሃድ

1. ስለባንኩ መፍረስና መዋሃድን በተመለከተ የንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች፣ በኢትዮጵያ ባንክ መመሪያ እና ሌሎች አግባብነት ባላቸውሕጎች መሰረት ተፈጻሚይሆናል፡፡
2. ባንኩን ለማፍረስ የተሾሙት የሒሳብ አጣሪዎች ተግባራቸውን አግባብነት ባላቸው የአገሪቱ ሕጎች መሰረት ማከናወን አለባቸው፡፡

## አንቀፅ 34

## የመመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻያ

የባለአክሲዮኖች አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ ይህንን የመመሥረቻ ጽሑፍ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## አንቀጽ 35

## የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ የመመስረቻ ጽሑፍ ከመፅደቁ በፊት በቀድሞ የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተከናወኑ ተግባሮች በሙሉ ህጋዊ ውጤታቸው የሚቀጥል ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 36

## የተሻሻለው መመሥረቻ ጽሑፉ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ የተሻሻለ የመመስረቻ ጽሑፍ በባለአክሲዮኖች 6ኛ አስቸኳይ ጠቅላላጉባዔ ጸድቆ በሚመለከተው የመንግስት አካል ከተመዘገበ በኋላ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

# የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ዝርዝር

**ይህ መመስርቻ ጽሑፍ በሚፀድቅበት ጊዜ ስራ ላይ ያሉ የቦርድ አባላት እና የአክስዮን ማህበሩ ፀሓፊ ዝርዝር**

| ተ.ቁ | ስም | ኃላፊነት | ፊርማ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዶ/ር ገብረህይወት አገባ ከበደው | የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ.ና እና የጉባኤው ሰብሳቢ. | |
| 2 | አቶ ፀጋይ ተጠምቀ ገ/እዝጊ | የዳይሬክተሮች ቦርድ ም/ሰብሳቢ. | |
| 3 | አቶ አለም አስፋው እሸት | ዳይሬክተር | |
| 4 | ወ/ሮ መዓዛ አለማየሁ ፍስሃ | ዳይሬክተር | |
| 5 | አቶ ሃይለ በርሀ ክንፈ | ዳይሬክተር | |
| 6 | ዶ/ር ፀጋብርሃን መኮንን ውቤ | ዳይሬክተር | |
| 7 | አቶ ፋሲል ታደሰ ሃይሉ | ዳይሬክተር | |
| 8 | አቶ ይርጋ ታደሰ ማቴዎስ | ዳይሬክተር | |
| 9 | አቶ አማኑኤል ካልአዩ ወከለ | የአክስዮን ማህበሩ ፀሐፊ | |